አሪፍ ነጋሪ የሚዲያ እና የመረጃ አጠቃቀም አጭር የቪዲዮ ውድድር

ኢንፎርም አፍሪካ ከአይ ኤም ኤስ ጋር በመተባበር በሚዲያ አጠቃቀም ላይ የሚያተኩር የአሪፍ ነጋሪ የአጭር ቪድዮ ውድድር አዘጋጅቷል።

እነዚህ ቪድዮዎች በየትኛውም አይነት አቀራረብ ከ 2 እስከ 4 ደቂቃ ለማኅበረሰቡ ስለሚዲያ እና መረጃ አጠቃቀም ክህሎት  ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ሆነው በድራማ፣ በአጭር ዶክመንተሪ፣ በስዕላዊ ቪዲዮ (Animation) እንዲሁም በሌሎች ሀሳቡን በሚገልፁ መንገዶች መቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

ጽንሰ ሐሳቦቹ፦

- ሚዲያ እና መረጃ አጠቃቀም ክህሎት (MIL)፡- የሚዲያ ይዘትን መመርመር፣ አዲስ የሚዲያ ይዘቶችን መፍጠር፣ መረጃዎችን በጥልቀት ማገናዘብ እና ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን የሚያስችል ችሎታ ማለት ነው። ይህንንም ለማሳካት የማገናዘብ ክህሎት (critical thinking) ጽንሰ-ሀሳቦችን ይጠቀማል።
- ሚዲያ እና መረጃ እንዴት እንረዳለን? መርጃዎችን ለመመርመርና ይዘቶችን ለመፍጠርና ለማጋራት ምን አይነት ክህሎቶችን እንጠቀማለን?
- የማገናዘብ ክህሎትን የሚዲያ ይዘቶችን ለመመዘንና ለመመርመር እንዴት እንጠቀማለን?
- የሚዲያ አጠቃቀም ክህሎት የማኅበረሰቡን የሚዲያና መረጃ ልምምድ ለማሻሻል እንዴት ይጠቅማል?

ስለ ጽንሰ-ሐሳቡ የበለጠ ለማወቅ.... ይጠቀሙ።

ውድድሩ ላይ የሚቀርቡ ቪዲዮዎች፡

- ለአሪፍ ነጋሪ ውድድር ብቻ ተብለው የተሰሩ መሆን አለባቸው።
- ከ 2 - 4 ደቂቃ ርዝመት ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል።
- ንግግር ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆን ይችላሉ።
- ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ የተሰሩ ቪዲዮዎች የአማርኛ ወይም የእንግሊዝኛ ፅሁፍ ትርጓሜ (Subtitle) ሊያካትቱ ይገባል።
- ማንኛውንም የቅጂ መብት ያለው ወይም የንግድ ምልክት የተደረገበትን ይዘት ካካተቱ እውቅና መስጠት ያስፈልጋል።
- ማንኛውንም ያልተፈቀደ ይዘት ካካተቱ ውድቅ ይሆናሉ።
- ጥራታቸውን የጠበቁ (High-definition- HD) መሆን አለባቸው።
- አጠር ያሉ ማብራሪያዎች እና ፖስተር ያስፈልጋቸዋል።

ሽልማት

1. አንደኛ ለወጣ፡ 35,000 ብር
2. ሁለተኛ ለወጣ፡ 20,000 ብር
3. ሶስተኛ ለወጣ፡ 10,000 ብር

ውድድሩ ላይ ለመሳተፍ፤ ስም ፣ ስልክ ቁጥር፣ ፖስተር፣ አጠር ያለ መግለጫ እና ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ቪዲዮ በኢንፎርም አፍሪካ የቴሌግራም አድራሻ @informafrica እስከ የካቲት 26 ብቻ መላክ ይቻላል።

ለማንኛውም ጥያቄ በስልክ ቁጥራችን 0930042578 ወይም በኢሜል አድራሻችን info@informafrica.net ያገኙናል።

የመጨረሻ አስር እጩ ተወዳዳሪዎችን ድህረ-ገጽ ላይ ይፋ ይደረጋል፤ እንዲሁም በስልክ የምናሳውቅ ይሆናል። ስለዚህ ትክክል ስልክ ማስገባቶን እርግጠኛ ይሁኑ።

አሸናፊዎቹ ቪዲዮዎች በተሻለ ሁነ ሁኔታ ለማኅበረሰቡ ስለሚዲያ እና መረጃ አጠቃቀም ክህሎት ግንዛቤ የሚያስጨብጡና በጥሩ አቀራረብ የተዘጋጁት ይሆናሉ።

አሸናፊዎች መጋቢት 10,2014 አሪፍ ነጋሪ በሚያዘጋጀው ፓናል ላይ ይፋ የሚደረጉ ይሆናሉ።